www.abyssinialaw.com



14ኛ ዓመት ቁጥር 9
14th Year No 9

ባህር ዳር ግንቦት 28 ቀን 2001 ዓ.ም
Bahir Dar 5th, June 2009

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA



| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 4.15 Price 4.15 | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ. 312 P.O.Box 312 |



## ማውጫ

ደንብ ቁጥር 67/2001 ዓ.ም
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የክልል መስተዳድር ም/ቤት አደረጃጀት፣ ስብሰባና ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት መወሰኛ ደንብ ቁጥር 3/1995 ዓ/ም (እንደተሻሻለ) ማሻሻያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ፣

## CONTENTS

Regulation No. 67/2009
The Amhara National Regional State the Council of Regional Government Organization, Meeting and Internal Working Procedure Determination Regulation No.3/2003 (as amended) Amendment, Council of Regional Government Regulation.

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የክልል መስተዳድር ም/ቤት አደረጃጀት፣ ስብሰባና ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት መወሰኛ ደንብ ቁጥር 3/1995 ዓ/ም (እንደተሻሻለ) ለማሻሻል የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ፣

## REGULATION NO. 67/2009

A REGULATION ISSUED BY THE COUNCIL REGIONAL GOVERNMENT TO PROVIDE FOR THE DETERMINATION OF AMENDING THE COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT ORGANIZATION, MEETING AND INTERNAL WORKING PROCEDURE REGULATION NO.3/2003 (AS AMENDED) IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

www.abyssinialaw.com



የአማራ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን ይህንን በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግስት የተጣለበትን ባለ ብዙ ፈርጅ ኃላፊነት ለመወጣት በየጊዜው የሚወያይባቸው አጀንዳዎች የክልሉን ልማት ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የሚጐለብትና ቀጣይነቱን የሚያረጋግጥ እንዲሆን በማስፈለጉ።

ይህንን ህገ-መንግስታዊ ሀላፊነት በብቃት ይወጣ ዘንድ ለመስተዳደር ም/ቤቱ የሚቀርቡ አጀንዳዎች ማሟላት የሚጠብቅባቸውን መስፈርቶች በህግ መደንገግና ሥራ ላይ ማዋል ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑን በመገንዘብ፣

በመሆኑም በሥራ ላይ ያለውን የመስተዳድር ም/ቤቱን አደረጃጀት፣ ስብሰባና ውስጣዊ የአሠራር ሥነ ሥርዓት መወሰኛ ደንብ እንደገና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ም/ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ- መንግስት አንቀፅ 58 አንቀፅ 7 እና በደንብ ቁጥር 3/1995 ዓ/ም (እንደተሻሻለ) አንቀፅ 33 ድንጋጌዎች ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአማራ ክልል መስተዳድር ም/ቤት አደረጃጀት፣ ስብሰባና የውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት መወሰኛ ደንብ ቁጥር 3/1995 ዓ.ም (እንደተሻሻለ)

WHEREAS, as the Council of Amhara Regional Government has been vested high executive powers and hence to discharge this multifaceted responsibility entrusted on it by the Revised Constitution of the National Region, it is necessary that agenda to be deliberated on from time to time by the council are to become the ones that development, democracy and good governance to be developed and its sustainability is materialized thereof.

Whereas, with a view to discharging this constitutional responsibility, it has been realized that it has great significance to stipulate and implement the required criteria for agendas to be presented to the council of the region;

Whereas, hence, it is found necessary to re-amend the existing council of regional government Organization, Meeting and Internal Working Procedure determination regulation thereof;

Now, therefore, the Council of the Amhara National Region, in accordance with the powers vested in it under the provisions of art. 58, sub. Art. 7 of the Revised National Regional Constitution and art. 33 of Regulation No.3/2003 (as amended), hereby issues this regulation.

## 1. Short Title

This regulation may be cited as "The Amhara Regional Government Organization, Meeting and Internal Working Procedure Determination Regulation No. 3/2003 (as amended)

www.abyssinialaw.com



ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 67/2001 ዓ./ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**2. ማሻሻያ**

የብሔራዊ ክልሉ መስተዳድር ም/ቤት አደረጃጀት፣ስብሰባና ውስጣዊ የአመራር ሥነ-ሥርዓት መወሰኛ ደንብ ቁጥር 3/1995 ዓ/ም (እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው በዚህ ደንብ ተሻሽሏል።

**የደንቡ አንቀፅ 13 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ 13 ተተክቷል።**

**አንቀፅ 13. ለመስተዳድር ም/ቤቱ የሚቀርቡ አጀንዳዎች ማሟላት ስለሚጠበቅባቸው መስፈርቶች፣**

1. የአጀንዳዎችን ቅርፅ ጥራትና ብቃት በተመለከተ ማንኛውም ለመስተዳድር ምክር ቤት እንዲቀርብ የሚላክ አጀንዳ የጉዳዩን ፍሬ ነገር፣ የጥናት አስተዋፅኦና ለውሣኔ የሚያስፈልጉትን የውሳኔ ሃሣቦች ማካተት ይጠበቅበታል፣ አጀንዳው የህግ ረቂቅ ማስፀደቅ ከሆነም የህግ ረቂቁን የአማርኛ ቅጂ የህጉን መንፈስ ከሚያስረዳ መግለጫ ጋር አብሮ መላክ ይኖርበታል፣
2. ከአጀንዳ ይዘት አኳያ አጀንደውን የሚልክ አካል የሚከተሉት የአጀንዳ ይዘት፣ ጥራትና ብቃት መስፈርቶች በአጀንዳው መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፣
   ሀ) አጀንዳዎች ከሀገራዊና ክልላዊ ፖሊሲዎች፣ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞችና አሠራሮች አንፃር የተጣጣሙ

amendment Regulation No.67/2009."

**2. Amendment**

The Council of Amhara National Regional Government Organization, Meeting and Internal Working Procedure Determination Regulation No. 3/2003 (as mended) has been amended under this regulation as follow.

**Article 13 of The Regulation has been repealed and replaced by new Article 13**

**Article 13. Criteria to be fulfilled for the Agendas that are to be presented to the Council of Government.**

1. With regard to form, quality and completeness of the agendas, any agenda that may be sent to be presented to the council of the government shall entail fact of the issue, study-contribution and decision-proposal necessary for making decision. If the agenda is about to ratifying a draft law, it shall be sent together with Amharic version of the draft law and a statement that explains the idea of the law.
3. with regard to content of an agenda, an organ that may send the agenda is bound to confirm that the following quality and completeness criteria for agenda content are fulfilled in the agenda:
   A. Examine that the Agendas are compatible with national and regional policies, programs and operations and their significance to implement

www.abyssinialaw.com



መሆናቸውንና እነዚህን ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ለማስፈፀም ያላቸውን ፋይዳ ፈትሾ ማቅረብ፣

ለ) በአጀንዳ ሰነዶች ላይ አግባብነት ያላቸውን ደንበኞችና አጋር አካላትን በተሟላ መንገድ ማሳተፍ፣ ማማከርና አስተያየታቸውን ተገቢነቱን መያዝና ማካተት ወይም ማስተናገድ፣

ሐ) ለም/ቤቱ የሚቀርቡ ጉዳዩች ከሌሎች ክልሎች ህዝቦች ጋር ያለውን መልካም ትስስር የሚያጠናክሩ መሆናቸውንና የአጋር አካላትን ተሞክሮዎች ግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን፣

መ) አጀንዳዎች ሲቀርቡ በተሟላ መረጃ ላይ የተመረኮዙ፣ የህዝብን ጥቅም ያገናዘቡ፣ ከወጡ አዋጆችና ደንቦች ጋር የተጣጣሙ ስለ መሆኑ፣

ሠ) ለም/ቤቱ የሚቀርቡ አጀንዳዎች መነሻ መግለጫዎችና አማራጭ የውሣኔ ሃሣቦች ላይ የታመነበትን አማራጭ ከነምክንያቱ ለይቶ ማካተት አለባቸው፣

ረ) ለመስተዳድር ም/ቤቱ የሚቀርቡ ጉዳዮች ከአቅራቢ ቢሮዎች የሥልጣን ክልል በላይ የሆኑና የም/ቤቱን ውሳኔ የሚፈልጉ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሰ) አስቸኳይና አስገዳጅ (በዕቅድ ወቅት ሊታዩ ከማይችሉ) ጉዳዩች በቀር ለመስተዳድር ም/ቤቱ ቀርበ እንዲወሰንላቸው የሚፈልጉትን አጀንዳዎች በም/ቤቱ ዕቅድ ማካተት፣

ተ) ደንበኞች ለውሣኔ የሚቀርቡ ህግ ነክ አጀንዳዎችን በፍትህ ቢሮ በኩል አረጋግጠ ማቅረብ፣

these policies and programs thereto; and thereby submit same to the council;

B. Make and consult customers and stakeholders participate fully on the agenda documents, and consider and entail or treat the appropriateness of their recommendations;

C. Issues to be presented to the council are to reinforce good linkage exists therein, with other regional peoples and whether or not it takes into account experience of stakeholders.

D. Where the agendas presented to the council are on the basis of complete information, consider people's interest and are compatible with the existing proclamations and regulations thereof.

E. Agendas to be presented to the council shall specifically entail initiative statement and acceptable proposal, with its reason, from among alternative decision-proposals thereof.

F. Ensure that issues to be presented to the council of regional Government are beyond the jurisdiction of presenter Bureau and thereby requires decision of the council.

G. Include to the plan of council the agendas presented to the council for decision thereof, with the exception of emergency and compulsory issues (that may not be viewed on schedule)

H. Customers (Bureaus) shall, having caused the verification of legal related agendas to be presented for decision through Justice Bureau, submit to the council

www.abyssinialaw.com



3. ማንኛውም አጀንዳ ለመስተዳድር ምክር ቤቱ ከመቅረቡ በፊት ወደ ጽ/ቤቱ መላክና የጥራትና ብቃት መስፈርቶችን ማሟላት ያለበት ሲሆን፣ ይህንን ስርዓት ጠብቆ ያልቀረበ አጀንዳ በቀጥታ ለም/ቤቱ ውይይት አይቀርብም፣

4. በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም ያመች ዘንድ እያንዳንዱ ደንበኛ አጀንዳ ሲልክ የሰነዱን የአማረኛ የወረቀት እና የኤሌክትሮኒክ ጨምሮ መላክ ይጠበቅበታል፣ እንዲሁም እያንዳንዱ መስሪያ ቤ ትየራሱ የሆነ የኤሌክትሮኒክስ አድራሻ ሊኖረውና ይኼንኑም ለጽ/ቤቱ ማሳወቅ ይኖርበታል።

## 3. ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ታይቶና ተመርምሮ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

ግንቦት ቀን 2001 ዓ.ም

አያሌው ጐበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር

3. Prior to its presentation to the council of regional government, any agenda shall be sent to the office and meet criteria of quality and completeness for agenda. Any agenda that is not presented following this procedure shall not be submitted to the council.

4. With a view to using modern information technology, each and every customer (Bureaus) shall send Amharic soft and hard copy of document of the agenda as well as each and every government office shall have its own e-mail address and notify same to the office thereof.

## 3. Effective Date

This regulation shall come into force as of the day of its deliberation upon and approved by the Council of the Regional Government.

Done at BahirDar

This 5th day of June, 2009

Ayalew Gobezie

Head of Government of the Amhara National Regional State